# መፈንቅለ ህዝባዊ መሻሻል (Revolution)

## መግቢያ

ትግል በሰዎች እንጂ በምኞት ወይም በእመነት አይካሄድም፡፡ ለህዝብ የሚጠቅም ትግል በአላሚዮች ብቻ አይካሄድም። ለህዝብ የሚጠቅም ትግል በሠራተኛ ግለሰቦች የሚሠራ ነዉ።

እነሆ መፈንቅለ ህዝባዊ መሻሻል (ሬቮሉሺን) ያመጡትን
ሦሥት እንቅስቃሤዎች  እንመልከት።

1. አንደኛዉ ትግል በእንግሊዝ ሕዝብ ወደ 1760 የተጀመረዉ ኢንዱስትሪአዊ ሬቮሊዩሺን ነዉ።
2. ሌላዉ ትግል ባ 1775 በአሜሪካ ተጀመሮ  ከቅኝ ገዥ እና  ከንጉሥ ሥራአት ተላቅቆ በሕግ የበላይነት መገዛትን ለማብሰር የተወሰድ እርምጃ ነዉ።
3. ሌላዉ ትግል ባ 1789 የፈረንሳይ ሬቮሊዩሺን ተጀምሮ ለሕዘብ የማይሠራን ሥነሥራአት ማስወገድ ነዉ፡፡

የተጠቀሱት ሬቮሉሺኖች በተቀራረብ ጊዜ ዉስጥ በተለያየ ቦታ ቢጀመሩም የአዉሮፓና የሰሜን አሜሪካን  ህዝቦች ኑሯቸዉን ለማሻሻል ጠቅሟቸዋል። ያለ ኢንዱስትራዊ ሬቮሉሺን ለውጥ አላሚዮችንና ተዋጊዮችን ብቻ  ይዞ መንቀሳቀስ በጠመንጃ የሚገዙ ወሮበላዎቸን ያስገኛል።

## በ 1776 የተጀመረው የእንግልዝ ህዘብ ኢንዱስትሪአዊ ሬቮሊዩሺን

በየባላገሩ የነበሩ ብረት ቀጥቃጮች፤ ወፍጮ ሠሪዎች፤ መስኖ ዉሃ ቦይ ሠሪዮች፤ ሸክላ እቃ ሠሪዮችና ሌሎቹም የግል ኑሯቸዉን ለማሸነፍ የሠሩትን ሌሎች እንዲገለገሉባቸዉ ይሸጣሉ። የእንግሊዝ ነገሥታትና ሹማምንቶቻቸዉ ቢደላቸዉም ባላገሩ የመረረና የከፋ ድህነት ያጠቃዉ ነበር። ባገሩ ሁለት ዩንቨርሲቲዮች ኬምበሪጅ እና  ኦክስፈርድ ቢኖሩም በዚያን ጊዜ መምህራኖች እዉነት መከተል ብቻ እንጂ ለህዝብ የሚጠቀም ጉዳይ ላይ ማተኮር ባህላቸዉ አልነበረም። ብዙሃኑ ወይ አልተማሩም አለበለዚያም የመጀመሪያ ደረጀ ትምህርት ቤት ብቻ የተማሩ ነበር። ከነሱ ዉስት ጀምስ ብሪንድሊ በዉሀ ኃይል እየተሽከረከረ የሚፈጭ ወፈጮ እሚሠራ ሱቅ ውስጥ ባ 17 አመቱ ስታፈርድሽር ባ 1733 ዓም  ተቀጥሮ ይሠራ ነበር። ወፈጮዎች በሚገባ ሰልተዉ የሸከላ አፈርን ለሸከላ ሠራተኞች እንዲአሙች እያደረገ ይሠራ ነበር። የመፍጫ መሳሪያዉን የሚሠራዉም ሌላ ወፍጮ ነዉ።  ይህነን ወፍጮ በደህና እንዲሽከረክር ፈጣን ዉሀ በቦይ መፍሰስ አለበት። ለዚህ ድርጊት እንዲአመች አቶ ብሪንድሊ የዉሀ ቦዮችን መቃኘት ይወድ ነበረ። ከዚያም ቦዮችን ለወፍጮ ብቻ ሳይሆን ማእድን

ለሚቆፈሩ ጭምር በመቃኘት የተሻል የውሀ ቦይ ይሥራ ጀመር። በቦይ ሥራ መልካም ስም ስላተረፈ ባካባቢዉ የነበሩ ብሪጅዋተር የሚባሉ መስፍን በቦይ ዉሀ የሚንሳፈፍ ጀልባ ላይ ከሰል ከአንዱ ቦታቸዉ እስከ ማንቼስተር ለመሸጥ እንዲአገዛቸዉ ተዋዋሉት። ማንቼስተር በዚያን ጊዜ ታዳጊ ትልቅ መንደር ሆኖ ወደ ደህና ከተማነት ሊቅየር የደረሰ ነበር። አቶ ብሪንድሊ የሥራዉ ቦይ በአንዳንድ ቦታ ከዛፍ ቁመት በላይ በድልድይ የሚያልፍ ሰልነበር በአካባቢዉ ያሉ ሁል ብ 1763 አም ይደነቁ ነበር። ከዚያም ማንቼስተርንና ሊቨርፑልን የሚአገናኝ የዉሀ ቦይ እንዲሠራና ተንሳፋፊ ጀልባ እንዲያልፈበት አቶ ብሪንድሊ በኮንትራት ሠራ። በጠቅላላዉ 400 ማይል ርዝመት ያላቸዉን ቦዮች አቶ ብሪንድሊ ሠርቷል። የእንግለዝ መንደሮች በቦይ ተገናኝተዉ ዉሀ የወፈጮንና የማእደን መሣሪዮችን ማንቀስቀሻ ኃይል ብቻ መሆኑ ቀርቶ የህዝብ ኑሮን ማሻሻያ የእንቅስቃሴ መገናኛ ሆነ።

ህዝቡ እህል፤ ከሰል፤ ሳህን፤ስኒ፤ አልጋ ሌልም ሸቀጣሸቀጥ ካንዱ መንደር ወደሌላዉ እየላከ መሸጥ ቻለ። እርስበርሱ በመነገድ ህዝቡ ኑሮዉን አሻሻለ። ቦዮቹ የተሠሩት በመንግሥት ትእዛዝ አልነበረም። ቦዮቹ የተሠሩት በለንደን ከተም ከሚገኙ አላሚዮች ታሰቦ አለንበረም። ቦዮቹ የተሠሩት ሥራ በሚያዉቁና ሥራቸው ለአካባቢያቸዉ አስፈላጊ ለሆኑ ጉዳዮች ነበር። አቶ ብሪንደሊ ዮኒቨርሲቲ የተመረቅ መሀንዲስ አለንበረም። ግን በድርጊቱ ስመ ጡሩ መሀንዲስ ነበር። ብሮናውስኪ (1973) እንዳስረደዉ አቶ ብሪንድሊን ብንጠቅሰም በቦይ ሥራም ሆነ በሌላ ተግባር ለህዘብ ግልጋሎት የተስማሩት እንግሊዞች የባልገር ሠራተኞች ነበሩ። የሁሉም የሥራ ዉጤት የህዝቡን ኖሮ የሚያሻሽል ነበር። እንግሊዘን በኢንዱስትሪ አሳደጉት። ሥራቸዉም ለሁብታሞች መዘናኛ መረከብ፤ ስአት እና የመሰሉትን ማበርከት ሳይሆን ለህዘቡ ጥቀም የሚሰጥ ነበር። በሌላ አዉሮፓ አገሮች ሥራቸዉ የተራቀቀ ሆኖ ጥቀሙ ለህበታሞች የሚያገለግል ነበር። እንዚያም ቢሆኑ ከህዘቡ የመጡ መሆናቸዉን አይረሱም ነበር።

በእንግልዝ የተጀመረዉ የኢንዱስቱራዊ ሬቮሉሺን ወደሌልች አገሮች ወደ አዉሮፓ እና አሜሪካ ተራብቷል።

<u>የአሜሪካንን የነጻነት ሬቮሉሺን</u>

ከእንግሊዝ ንጉሥ ሳልሳዉ ጆርጅ ነጻነታቸዉን ለማግኘት የአሜሪካ ገበሬ፤ ጠበቃ፤ ብረት ቀትቃጭ፤ ወፍጮ ፈጪ፤ በጠቅላላ ህዝቡ በ 1775 ጦርነት ከፈቶ ከአመት በኋላ የ 13 ስቶቲቶች ወካዮች የአህጉር ጉባኤ (ኮንግሪስ) ፊላደለፊያ ላይ ተሰበስበዉ የነጻነታቸዉን መግልጫ ዉል በ ጁልይ 4/ 1776 ዓም አወጁ፡፡

“እንኝህን እዉነቶች በራሳቸዉ ግልጽ እንደሆኑ እናምናለን፤ ሰዎች ሁል እኩል ሆነዉ መወለዳቸዉን፤ ፈጣሪያቸዉም ከነሱ ሊገነጠሉ የማይገቡ መብቶች ስጥቷቸውል፤ ከነዚህም ዉስት ህይወት፤ ነጻነትና ደስታን መሻት ናቸዉ። -እንኚህን መብቶች

ለመጠበቅ፤ መንግሥታት በህዝቦች መካከል ይቋቋማሉ፤ የፍትህ ኃይላቸዉን ከሚያአስተዳደሩት ሰዎች አገኝተዉ - እናም በማንኛዉም ጊዜ ማንኛዉም መንግሥት እነኚህን ግቦች የሚአፈርስ ቢሆን ህዝቦቹ መብታቸዉን ተጥቅመዉ መቀየር ወይም ማዉደም እና መሰረቱንና ኃይሉን አዋቅረዉ የነሱን ደህነንትንና ደስታን ሊሰጥ የሚችል አዲስ መንግሥት ማቋቋም መብታቸዉ ነዉ።"

ይህ አገላልጽ ያለበትን የአሜሪካን ነጻነት መግልጫ የደርሰዉ አቶ ቶማስ ጀፈርሰን ነበር። መግለጪያው እጉባኤ ከምግባቱ በፊት አቶ ጆን አዳምስ እና አቶ ቤንጃሚን ፍራንክሊን (የ 70 አመት ሽማግሌ) ማሽሻያ አድርግዉብት ነበር። ከዚያም ጉባኤ ከሰምምነት ዉጪ የነበሩ ጽሁፎችን አስወገዱል።

በሴፐቴምበር 17/ 1778 ዓም የአሜሪካ ኮንስቲቱዩሺን በፊላደለፊያ በኮንስቲቱሽን ኮንቬንሺን (ኮንግሪስ) ጸደቀ። ከዚያም በየስቴቶቹ ኮንግሬስ ጸደቅ። ኮንስቲቱሺኑ ሦሥት ከፍል ያለው መንገሥት፤ ሕግ አዉጪ (ኮንገሥ እና ሴናት)፤ ሕግ አሰፈጻሚ (ፐረዚዳንቱን የሱ ካቢኔት) እና ሕግ ተርጓሚ (ሱፐረመ ኮርት እና ከሱ በታች ያሉ ዳኞች) አቋቋመ። የአሜሪካ ኮንስቲቱዩሺን በሀገሩ ያሉትን የደንቦች እና ሕግጋት የበላይ ነዉ።

የአሚሪካ የነጻነት በሕግ የበላይነት መገዛትን የመረጠ የህዘብ ትግል ዉጤት ነዉ።

<u>የፈረንሳይ የነጻነት ሬቮሉሺን (1789-1792)</u>
በእንግሊዝ የተጀመረውይ የኢንዱስቱራዊ ሬቮሉሺን በአሜሪካም የተኬሄደዉ የነጻነት ትግል በፈርንሳይም ተራበቷል።

በፈረንሳይ አቶ ፒየር ካሮን ብላሃትኛ ሰአት ሠሪ ነበር። የፈጠርዉን ሰአት ለንግሥት ሜሪ አትዋኔት አበረከት;። እሷም ስለተደሰተች አቶ ፒየርን ኮንት ቦማርሼዪ ብላ ሰየመችዉ። ቦማርሼዪ የሙዚቃ እና የደራሲነት ጥበበ በተጨማሪ ነበረዉ። *የፊዩግሮ ጋብቻ* የተሰኘ ጽሁፍን አዘጋጂቶ አሸከርዩዉ ፊዩገሮ የሬቮሉሺነሪ መንፈስ እንዲኖረዉ አደርጎ ጻፈ፡፡

" አይሆንም ጌታዬ ኮንት የአንተ አትሆንም፤ አታገባትም። ትልቅ ጌታ በመሆንህ ትልቅ ሊቅ የሆንክ መስሎሃል። ከጌቶች መወልድ፤ ሀብት፤ ክብር፤ መመስግን! እነኚህ ሁል ሰዉን ያኮሩታል። እነኚህን ሁል አጋጣሚዮች እንደታገኝ አንተ ምን አድርገሃል? የነበረበህ ችግር ከዚያ ቤት መወልድ ብቻ ነበር። ሌላ ተጨማሪ ድርጊት አልሠራህም። ከዚህ ድርጊትህ ዉጪ አንተ እንደማንኛዉ አይነት ነህ።" (ብሮናዊስኪ፣ 1973)

ይህን አገላልጽ ያዘለ ጹሁፉ በ 1780 ቢጨርስም ተፈቅዶለት የታተመው ከአራት አመት በኋላ በ 1784 ዓም ነበር። በ 1786 ጽሁፉን ሞዛርት በኦስትሪያ ወደ ኦፔራ

ቀየረው። ሞዛርት በሀገሩ በኦስትሪያ የነበረዉን ሥንሥራትና ሃይማኖት ስለማይወድ በ 1791 ሲሞት ፍትሐት አላገኘም ነበር። በፈርንሳይ የቦማርሼዬ ድርሰት የንጉሥ 16ኛ ሉዊ ተቃዋሚዮችን አስደስቶ ነበር።

የኦስትሪያ ንጉሥ ልጅ ማሪያ አትዋኔት ባ 14 አመቷ የፈረንሳ የንጉሥ ልጅ አግብታ ባሏ በ ሜይ 17/ 1774 የፈርንሳይ ንጉሥ 16ኛ ሉዊ ሲባል እሷም የፈረንሳይ እና የናቫሪ ንግሥት ተባልች። ህዝቡ በኑሮዉ ስላልተደሰት እና ርሃብም ሰላስቸገረዉ ከ 1789 ጀመሮ የህዝብ ወካዮች የንጉሡን ስለጣን እይቀነሱ የነሱን እያበዙ፤ ከዚያም ሀገራዊ ወታደር እያቋቋሙ መምጣታቸዉ ብቻ ሳይሆን ቤተመንግሥቱን በአካፋን በዶም ጭምር ህዝቡ ወረረዉ። የንጉሡም ቤተሰብ ታሠረ። ንጉሥ ሉዊ አንገቱን ተቁርጦ ተገደለ። ባልቤቱም ንግሥት አትዋኔት ባሏ ከተገደለ ከዘጠኝ ወር በኋል በ 16 ኦክቶበር 1793 ዓም አንገቷን ቆርጠዉ ገደሏት። የፈረንሳይ ሪፓብሊክ ተቋቋመ።

የፈረንሳይ ህዘብ ያደርገዉ መፈንቀለ መንግሥት ያውሮፓን ወጣት ምሁራኖች በእጃቱ ማርኮ ነበር። አንድ ሃሳብ (ቲሲስ) ተቃዋሚ ይኖረዉና (አንቲቲሲስ) የሁልቱ ሃሳቦች መቃረን ሌላ ሃሳብ ይወልዳል (ሲንቴሲስ)። እንዲህ አየንቱ ዳያሌክትክስ ፈላስፋዉ ጆርጅ ዊልሄልም ፍሬደሪክ ሄግል በሰዎች ኑር ዉስት ያለዉን ቅራኔና ችግር ያሳያል ብሎ ገለጸ። ከዚያም እድሜው ወደ 20 አመት ገደማ በነበረበት ጊዜ ሄግል የፈረንሳይ ህዝባዊ ሬቮሉሺን ለሰዉ ልጅ ዳያሊክትካዊ ችግር የመጨረሻ መፍትሄ ስጥቷል ብሎ ነበር። በእደሚዉ እይጠና ሲሄደ ግን የሰዉን ችግር የመጨረሻ መፍትሄ የሰጠዉ የፕራሺያ ሥነሥራት ነዉ በማለት የጀርመንን መኳንነት አስደስቶ ነበር።

ካርል ማርክስ ዳያለክቲካዊ አስተሳሰቡ ቢአስደስትዉም ሃስብ የህዝብ ኑሮ ለውጥ ያመጣል የተሰኘዉን የሄግል እይታ ጉዳዩን ባስጢሙ ደፍቶታል ብሏል። በቀጥታ ብነመለከተዉ ግን፤ አለ ማርክስ፤ ቅርኔና የቀራኔ ዉጤት የሚያመጣዉን ለዉጥ የሚያስረዳዉ ዳያለክቲካዊ ማቴሪያሊዝም ነዉ። በዚህም መሠረት ለሰዉ ልጅ ችግር የመጨረሻ መፍትሄዉ የሚሆነዉ ግለሰቡ ባበረከትዉ ሥራ መጠን ሲከፈለዉ (በሶሺአሊዝም) እና ግለሰቡ እንደሚአስፈልገዉ ጥቅም ሲያገኝ (በኮሚኒዝም) ነዉ ብሎ ማርክስ ደነገገ። ከዚያም በሃስብ የተመረኮዘ ሳይሆን ዳያለክቲካዊ ማቴሪያሊዝምን ማርክስ የፈጥረዉ በሰውች ግንኙነት ላይ ግንዛቤ አድርጎ በመሆኑ ዳያለክቲካዊ ማቴሪያሊዝም ስይንቲፊክ ነዉ ብሎ አወጀ። እነሆ ኮሙኒዝም የታርክ መጨረሻ ነው ተባል። በመካከለኛዉ እና በሩቅ ምስራቅ እንዲሁም ባፍሪካ እና በደቡብ አሜሪካ የሚገኙ አንዳንድ ሀገሮች ሶሺአያልዝምንና ኮሚንዝምን ለማምጣት ታገሉ።

ሀጊ-